# ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ

ጌታሁን ወርቁ

በአሁኑ ወቅት አዘውትረው ከሚነገሩት ቃላት ውስጥ ‹‹ሰብዓዊ መብት›› የሚለው ሰዎች ሰው በመሆናቸው መንግሥታት ሊጠብቁላቸው የሚገቡ መብቶች እጅጉን የታወቁት ናቸው፡፡ ሰብዓዊ መብት አለ ብሎ በሚጠይቀውም፣ መብት ረገጠ በሚል በሚከሰሰውም አካል በተደጋጋሚ በመከላከያነት ወይም በማስረጃነት የሚጠየቅ ነው፡፡ በየዕለቱ ከምናስተውለው የሰው አኗኗር የሰብዓዊ መብት ጥያቄ የማይነሳበት ጉዳይ የለም ቢባል ሁሉንም የሚያስማማ ሐቅ ነው፡፡ ስለሴት ልጅ ጥቃት፣ ስለመረጃ ነፃነት፣ ስለምርጫ፣ ስለሰላማዊ ሰልፍ ወዘተ የምናነሳቸው ወቅታዊ ጉዳዮች በሙሉ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ይዘት፣ ስፋትና ወሰን የሚነሳባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

የሰብዓዊ መብት ቀን በየዓመቱ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 10 ቀን የሚከበር ሲሆን፣ ዘንድሮ ለ 66 ኛ ጊዜ ባለፈው ሳምንት ተከብሯል፡፡ ዕለቱ እ.ኤ.አ. በ 1948 የፀደቀው የተባበሩት መንግሥታት ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) የሚታሰብበት ዕለት ነው፡፡ ዘንድሮ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰብዓዊ መብት ማዕከል ዕለቱን በዓውደ ጥናት ያሰበው ሲሆን፣ ሰብዓዊ መብቶችን ከተለያዩ የሙያ መስኮች አንፃር በመቃኘት የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች በምሁራን ቀርበዋል፡፡ ይህ ጽሑፍ የጉባዔውን ውሎ መዘገብ ባይሆንም በዓለም ገኘ ከሆኑት ሰነዶች መሀል የሚመደበውን ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫን ማስተዋወቅ ነው፡፡ መግለጫው እንዴት ተቀረፀ? ምን ይዘት አለው? ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ምን ጥቅም አስገኘ? በሒደት ምን ተግዳሮቶች አጋጠመው? የሚሉትን ጠቅላላ ነጥቦች በመዳሰስ ስለመግለጫው የተወሰነ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይሞከራል፡፡

## ታሪካዊ ዳራ

በሰው ልጆች ታሪክ ከማይረሱት ዘግናኝ ክስተቶች መካከል ዋናው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ነው፡፡ በተለያዩ የዓለም ክፍል የሚኖሩ ሕዝቦች እንዲሰቃዩ፣ እንዲጨቆኑና እንዲጨፈጨፉ ተደርገዋል፡፡ ይህ ታሪካዊ ክስተት ዳግም እንዳይከሰት በማሰብ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እ.ኤ.አ. በ 1945 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታትን ያቋቋሙ ሲሆን፣ የተቋሙ ቻርተር የግለሰቦች ሰብዓዊ መብት እንዲከበርና አገሮች በሰላም እንዲኖሩ መሠረት ጥሏል፡፡ በቻርተሩ ሰፊ ቦታ ያልተሰጠው የሰብዓዊ መብት በዝርዝር እንዲደነገግ፣ እንዲታወቅና የሕግ ዋስትና እንዲያገኝ የተባበሩት መንግሥታት ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብት መግለጫ ተዘጋጅቶ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 10 ቀን 1948 በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ፀድቋል፡፡ መግለጫውን ደግፈው ካፀደቁት የአፍሪካ አገሮች መካከል ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ላይቤሪያ ይገኙበታል፡፡ ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ የዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ሕግ መሠረት ነው፡፡ ሰነዱን ለማርቀቅ የተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሰብሳቢ የነበሩት ኦሪነር ሩዝቬልት ሰነዱን የሰብዕና ማግና ካርታ (Humanity's Magna Carta) ሲሉ ሰይመውታል፡፡ የዓለም ድንቅ ነገሮችን የሚዘግበው የጊነስ ቡክ ኦፍ ሪከርድስ መግለጫውን በዓለም በመተርጐም ብዛት ወደር የማይገኝለት ሰነድ በሚል መዝግቦታል፡፡

የመግለጫው ይዘት

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የታየው ሰፊና ወጥነት ያለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሰነዱን ዝግጅት ለመጀመር አስገዳጅ ምክንያት በመሆኑ፣ በጊዜው የተከናወኑ ክስተቶች ይዘቱን ለመወሰን የሞራል መሠረት ሆነዋል፡፡ መግለጫው በዋናነት በሁለት አንኳር ነጥቦች ላይ እንዲያተኩር የታለመ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ተፈጥሯዊ ለሆነው ለሰው ልጅ ክብር (Dignity) እውቅና የመስጠት ቁርጠኝነት ሲሆን፣ ሌላው መድልኦን በማስወገድ ሰዎች በእኩልነት የሚኖሩበትን ሁኔታ ማስፈን ነበር፡፡ ሰነዱን በመጀመሪያ ያዘጋጀው ካናዳዊው ጆን ፒተርስ ሀንፍሬ ሲሆን፣ ሁለተኛውን ረቂቅ ቅርጽ ያስያዘው ደግሞ ፈረንሳዊው ሆኔ ካሲን ነው፡፡ የድንጋጌዎቹ ቅርጾች በናፖሊዮን ኮድ ተፅዕኖ የተደረገባቸው ሲሆን፣ በተለይ ይህ ተፅዕኖ በመግቢያውና በይዘቱ በተካተቱ መርሆች ተንፀባርቋል፡፡ የመግለጫው መግቢያ የሰነዱን ዓላማ የሚዘረዝር ሲሆን፣ መግለጫው የሰዎችን ተፈጥሯዊ ክብር እውቅና መስጠት፣ የሰዎችን እኩልነትና የማይገሰስ መብት በማክበር ዓለም ላይ ነፃነት፣ ፍትሕና ሰላም ማምጣት እንደሆነ ይገልጻል፡፡

የመግለጫው አንቀጽ 1 የመግለጫውን ተስፋ የያዘ ሲሆን፣ <<ሁሉም ሰው ነፃ ሆኖ የተፈጠረና በእኩልነት ክብርና መብት ይገባዋል፡፡ ሁሉም ሰው ምክንያትና ህሊና በተፈጥሮ የተሰጠው በመሆኑ አንዱ ለሌላው በወንድማማችነት መንፈስ ሊግባቡ ይገባል፤>> በሚል ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ የሰብዓዊ መብት መሠረት የሆነውን የሰውን ልጅ ክቡርነትን እውቅና የሰጠ ሲሆን፣ መድሎአዊነትን በመከልከል ሁሉም ሰው እኩል መሆኑን እውቅና በሚሰጠው የመግለጫው አንቀጽ 7 አጽንኦት የተሰጠው ነው፡፡

የመግለጫው አንቀጽ 3 እና 27 የመግለጫው ዋና ክፍል ሊባሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ አንቀጽ 3 የማንኛውንም ሰው በሕይወት፣ በነፃነትና በደኅንነት መኖር እውቅና ሲሰጥ አንቀጽ 27 ደግሞ የሰዎችን ተገቢ የሆነ አኗኗር (Adequate Standard of Living) እውቅና ሰጥቷል፡፡ የመግለጫው መጀመሪያ ሦስት አናቅጽ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችን የሚመለከቱ ሲሆን፣ የመጨረሻዎቹ ሦስት ደግሞ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መብቶችን እውቅና ይሰጣሉ፡፡ የተስተካከለ ኑሮ የጤና፣ የምግብ፣ የልብስ፣ የመጠለያና የማኅበራዊ ዋስትና መብቶችን ለግለሰብና ለቤተሰቡ ዋስትና የሚሰጥ ነው፡፡ የመግለጫው አንቀጽ 28 እና 29 የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሰዎችን የሰብዓዊ መብት እንዲያከብሩ የሚጠይቁ ድንጋጌዎች ሲሆኑ፣ አንቀጽ 30 ደግሞ ሰዎች ለኅብረተሰባቸው ያለባቸውን ኃላፊነት የሚደነግግ ነው፡፡

የመግለጫው ጠቃሚነት

ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ሰብዓዊ መብትን ትርጉም በመስጠት፣ መብቶቹን በመዘርዘር እንዲሁም በቀጣይነት ለወጡት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች መሠረት በመሆን ዓብይ ሚና ተጫውቷል፡፡ በመግለጫው መግቢያ ላይ እንደተገለጸው አገሮች በኅብረተሰባቸው ውስጥ የሰዎችን የሰብዓዊ መብት ለማክበር ግዴታ መግባታቸው አገሮች ለሰብዓዊ መብት መጠበቅ ቁርጠኛ ለመሆን የሚያነሳሳቸው መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ መግለጫው ሕጋዊ አስገዳጅነት ባይኖረውም በዓለም መንግሥታት እውቅና አግኝቶ በፀደቀበት መጠን ብሔራዊ ሕግጋት መንግሥታት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ለምሳሌ የአገራችንን ታሪካዊ ሁኔታ ብንመረምር መግለጫው የ 1955 ሕገ መንግስት የሰብዓዊ መብቶችንና ነፃነቶችን እንዲዝ ተፅዕኖ አድርጓል፡፡ ይህም የሚያመለክተው

አገሮች ዴሞክራሲያዊ ይሁኑ ፈላጭ ቆራጭ በወቅቱ የሰብዓዊ መብቶችን በሕገ መንግሥታቸው የማካተት ልማድን አክብረው ነበር፡፡

መግለጫው እንደፀደቀ የመግለጫው ዓብይ ችግር ተደርጐ ይወሰድ የነበረው አስገዳጅ ያለመሆኑ ነገር ነበር፡፡ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥታት ሳይቀሩ በሰነዱ የተካተቱ መብቶች የውስጥ ጉዳያችንን ይረብሻል በማለት ባይደግፉት እንኳን አስገዳጅ ባለመሆኑ ተቀብለውት ነበር፡፡ ዴሞክራሲያዊ አገሮች ደግሞ አስገዳጅ ግዴታዎችን በመንግሥታት ላይ አለመጣሉ በቀላሉ የሚጣስ ሰነድ እንደሆነ ያምኑ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቱ የነበሩት አንዳንድ ምሁራን ሩዝቬልትን ጨምሮ የመግለጫው ባህርይው ለመለወጥ የሚመች (Flexible) መሆኑ የሰብዓዊ መብትን ለማስፋፋት ለሚቀረጹ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ሰፊ ቦታ የሚሰጥ ከጊዜያት በኋላ ለወጡት አስገዳጅ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች እንደ መነሻ ማገልገሉን እንደ እመርታ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መግለጫው በተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ክፍሎችና ኤጀንሲዎች ውሳኔ የተጠናከሩ ሲሆን፣ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው በአገሮች ብሔራዊ ሕግጋት መንግሥታትም ውስጥ ሊካተቱ ችለዋል፡፡ እነዚህ ለውጦች መግለጫው አስገዳጅ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች እንደ መነሻ ማገልገሉን ያነሳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መግለጫው በተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ክፍሎችና ኤጀንሲዎች ውሳኔ የተጠናከሩ ሲሆን፣ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው በአገሮች ብሔራዊ ሕግጋት መንግሥታትም ውስጥ ሊካተቱ ችለዋል፡፡ እነዚህ ለውጦች መግለጫው አስገዳጅ ባይሆንም በጊዜ ሒደት በተሰጡ የፍርድ ቤቶች ውሳኔና የአገሮች ተግባራዊ ተሞክሮ መግለጫው ልማዳዊ የዓለም አቀፍ ሕግጋትን (Customary International Law) ቦታን እንዲገኝ እንደረዳው የሰብዓዊ መብት ምሁራን ይስማማሉ፡፡ ልማዳዊ የዓለም አቀፍ ሕግ አገሮች የሰነዱ ፈራሚ/አፅዳቂ ባይሆኑም በሰነዱ የሚገደዱበት የሕግ መርህ በመሆኑ፣ መግለጫውን ያልደገፉ አገሮች ሳይቀር በመግለጫው ይዘት የተካተቱትን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ መግለጫው በጊዜው ከዳበሩት የዓለም አቀፍ ሕግጋት በተሻለ የግለሰቦችን መብቶች እውቅና በመስጠትና የሰብዓዊ መብትን በሁሉም ተቀባይነት እንዲያገኝ የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ሆኖም በይዘቱ የሰብዓዊ መብቶችን የሚጥሱት መንግሥታት ብቻ እንደሆኑ በሚያስብ መነሻ መቀረጹ ከመንግሥታት ውጭ ያሉ አካላት (Non-State Actors) ግለሰቦች፣ ቤተሰብ፣ ኅብረተሰብና ሌሎች የግል ተቋማትን ከኃላፊነት የማግለል ክፍተት እንዳለበት አንዳንድ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

መግለጫው ያጋጠሙት ተግዳሮቶች

መግለጫው የጠቃሚነቱን ያህል በተግባር በሁሉም አገሮች በእኩል እንዳይከበር የተለያዩ ተግዳሮቶች ገጥመውታል፡፡ ተግዳሮቱ የጀመረው መግለጫውን ከማዘጋጀት ሒደት ጀምሮ ሲሆን፣ በጊዜው የተነሱት አከራካሪ ነጥቦች እስካሁን ድረስ ምሁራንን በድጋፍና በተቃውሞ ልዩነታቸውን እያንፀባረቁ እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል፡፡ መግለጫው በሚዘጋጅበት ወቅት አከራካሪ የነበሩ ብዙ ጭብጦች እንደነበሩ በመግለጫው ላይ የተጻፉ ዋቢዎች ይተነትናሉ፡፡ የሰው ክቡርነት ትርጉም፣ የሰብዓዊ መብቶችን ይዘትና ስፋት ለመወሰን ተፅዕኖ ስለሚኖራቸው ሁኔታዎች (ለምሳሌ ባህል)፣ ግለሰብ ከመንግሥትና ከኅብረተሰቡ ጋር ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንኙነት፣ የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች ከሉዓላዊነት ሥልጣን ጋር በተያያዘ ሊኖር ስለሚችል ተግዳሮት፣ መብትና ግዴታ/ኃላፊነት ስለሚኖራቸው ግንኙነት፣ በግላዊና ማኅበራዊ ደኅንነት መንፈሳዊ እሴቶች ያላቸው ቦታ አከራካሪ ከነበሩት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

እስካሁን ድረስ በመግለጫው ላይ ከተጋረጡት ተግዳሮቶች ግን የሰብዓዊ መብቶችን ሁሉ አቀፍነት የሚቃወሙ አካላት ባህልን መሠረት አድርገው የሚያነሱዋቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ነጥቦች መግለጫው በሚረቀቅበት ወቅት የነበሩ የፖለቲካዊና አይዲኦሎጂአዊ የሐሳብ ልዩነቶች ነፀብራቅ ናቸው፡፡ ክርክሩ ሁለት የተለያዩ ጠርዞችን የያዘ ነው፡፡ የሰብዓዊ መብቶችን ሁሉ አቀፍነት የሚቀበሉ ወገኖች (Universal) ሰብዓዊ መብት አንድ ሁሉንም የሚያስማማና ሁሉ አቀፍ ነው ይላሉ፡፡ ይህ አስተሳሰብ መነሻ የሚያደርገው ሰብዓዊ መብት ሁሉ አቀፍ ክስተት ሲሆን፣ ትልቅ ማኅበራዊ ግብን ለማሳካት እንደ መሣሪያ የሚጠቅሙ ናቸው የሚል ነው፡፡ ሰብዓዊ መብቶች መሠረታዊና በሁሉም ኅብረተሰብ የሚታወቁ፣ ከሰው ተፈጥሯዊ ክብር የሚመነጩ፣ ሰዎች ሴት ቢሆኑ ወንድ፣ ሀብታም ቢሆኑ ድሃ፣ አማኝ ቢሆኑ እምነት ባይኖራቸው ሰው በመሆናቸው ብቻ ያሏቸው መብቶች ናቸው በሚል ሁሉ አቀፍነታቸውን ያምናሉ፡፡

ሌሎች ደግሞ (Cultural Relativism) ዓለም የሰዎች፣ የባህል፣ የትውፊትና የሃይማኖት ልዩነት የሚንፀባረቅባት እንደመሆኗ መጠን ትውፊታዊ፣ ባህላዊ እሴቶች የአገሮችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አመለካከትንና ፍላጐትን ይወስናል ይላሉ፡፡ ለእነዚህ አካላት ሰብዓዊ መብቶችን የሚወስነው ኅብረተሰቡ እንጅ ግለሰብ አይደለም፡፡ እሴቶች በባህል እንደሚለያዩ ሁሉ ሰብዓዊ መብትን ባህልን መሠረት አድርጐ መቃኘት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በመነሳት ተቃዋሚዎቹ ሰብዓዊ መብት አንድና ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር ያስቀምጣሉ፡፡ በተጨማሪም በመግለጫው ላይ የተደነገጉት የሰብዓዊ መብቶች ግለሰቦችን ማዕከል ያደረገ፣ የምዕራባውያን አስተሳሰብ ነፀብራቅ ነው ሲሉ ያጣጥሉታል፡፡ ይህ አስተሳሰብ በጊዜው መግለጫው ከጦርነቱ በኋላ የተባበሩት መንግሥታትን ሲረቀቅ የአፍሪካና የእስያ አገሮች ያልተሳተፉበት፣ ምዕራባውያኑ የጊዜውን መድረክ ተቆጣጥረው ያወጡት መሆኑን መነሻ በማድረግ የሰነዱን ዋጋ ዝቅ ለማድረግ የሚያቀነቅኑ ምሁራን አሉ፡፡

ክርክሩ ሥር የሰደደ ቢሆንም የሁለቱ ሙግት የሰብዓዊ መብቶችን ዋጋ የሚያሳጣ አይደለም፡፡ የመግለጫውን ይዘት ለመረመረ የተዘረዘሩት መብቶች ከመሠረታዊ የፍትሕ፣ የሰው ክቡርነት፣ ወዘተ መርሆች የሚመነጩ እንደመሆናቸው በማንኛውም ኅብረተሰብ ክፍል በጋራ የሚታወቁና የሚከበሩ ናቸው፡፡ ሰብዓዊ መብቶች በሒደት የዳበሩት ለፍትሕ፣ ለሰላምና ለመቻቻል መሠረታዊ መርሆችን ለማስቀመጥ በተደረገ ጥረት ነው፡፡ ሰብዓዊ መብቶች የተለያዩ የባህልና የፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታዎች ባሉበት ሁኔታ የማኅበራዊ ትስስርን ለማጠናከር የሚረዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሰብዓዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የአገሮችን ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ የሥነ ጾታና ሌሎች ሁኔታዎችን ግንዛቤ ያላስገቡ ሊሆኑ አይገባም፡፡ የሰብዓዊ መብቶች በማንኛውም ኅብረተሰብ መፈጸም የሚችሉ፣ ከማንኛውም ማኅበራዊ ጭብጥ (ጉዳይ) ጋር በቁርኝት ሊካተቱ የሚችሉና የሚለዋወጡ (Flexible) መሆናቸው መዘንጋት እንደማይገባቸው የሁለቱን ጠርዝ አቋሞች ለማስታረቅ የሚጥሩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ሰብዓዊ መብቶች በአንድ በኩል ያልተገቡ ባህሎችን የሚያስወግዱና ሁሉ አቀፍ የሆነውን የሰው ክቡርነትን የሚያሰፍኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ኅብረተሰቦችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች የሚያከብሩ መሆናቸው መዘንጋት የለበትም፡፡ በዘመነ ሉዓላዊነት (Globalization) የቴክኖሎጂ ዕድገትና የመረጃ ፍሰት፣ የባህል ልዩነቶች ቀስ በቀስ ጠቀሜታቸውን እያሳጡ እያስተዋልን በመሆኑ በጊዜ ሒደት የሰብዓዊ መብቶች ባህል ሊተካቸው እንደሚችል ማሰብ ብልህነት ነው፡፡

እንደ ማጠቃለያ

ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ በተባበሩት መንግሥታት ከወጡ ሰነዶች በሙሉ ከፍ ያለ ከበሬታ ያለው የሰዎችን መብቶችና ነፃነቶች በምልዓት፣ በዓይነትና በዝርዝር የገለጸ ሰነድ ነው፡፡ ሰነዱ ከፀደቀበት ከዲሴምበር 10 ቀን 1948 ጀምሮ ባለፉት 66 ዓመታት ለብሔራዊ ሕግጋተ መንግሥታት መሠረት በመሆን የሰብዓዊ መብት አነስተኛ መሥፈርት (Standard) በመሆን አገልግሏል፡፡ በተባበሩት መንግሥታት በተለያዩ ጊዜያት ለተቀረጹት የሰብዓዊ ስምምነቶችም ሆነ በአኅጉራት ለተቀረጹት ክልላዊ ሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች መሠረት በመሆኑ መግለጫው ታላቅ ሰነድ መሆኑ በሁሉም አካላት የታወቀ ነው፡፡ መግለጫው እንደ ኮንቬንሽን ሕጋዊ አስገዳጅነት እንዲኖረው ተደርጐ ባይቀረጽም፣ ባለፉት 66 ዓመታት ባገኘው ተቀባይነት ዓለም አቀፍ የልማዳዊ ሕግ በመሆን ያልተቀበሉትንም አገሮች የማስገደድ ባህርይ አግኝቷል፡፡ ከባህል አንፃር መግለጫው ወይም ሰብዓዊ መብቶች ባጠቃላይ የሚነሳባቸው ትችትም ቢሆን የአይዲኦሎጂ ልዩነት ነፀብራቅ ከመሆን ውጭ በመግለጫው እውቅና ያገኙትን ከሰው ክቡርነት የሚመነጩ መብቶች ዋጋ የሚያሳጣ አይሆንም፡፡

አንዳንድ የአፍሪካ ምሁራን መግለጫው በአፍሪካ ቻርተር እንዳካተተው ዓይነት የብዙኃን የቡድን መብት አለመያዙን ይተቻሉ፡፡ ይሁን እንጂ መግለጫው ሁሉን አቀፍ እሴቶችን የያዘ ቢሆንም ያልተሟላ እንደሆነ ሊታሰብ ይገባዋል፡፡ ይህንንም የአፍሪካ አኅጉራዊ የሰብዓዊ ስምምነቶች ከመግለጫው ይዘት ላይ በመጨመር የመግለጫውን ይዘት የሚያስቀር ወይም የሚለውጥ አለመሆኑን በተግባር አሳይተዋል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ መግለጫውን ካፀደቁት ሦስት የአፍሪካ አገሮች አንዷ ከመሆኗ በተጨማሪ በተለያዩ ዘመናት በወጡት ሕግጋት መንግሥታት እንዲካተቱ አድርጋለች፡፡ በአሁኑ ወቅት ተፈጻሚ በሆነው የ 1987 ዓ.ም. የወጣው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ሁሉ አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ አካል ያደረጋቸው ሲሆን፣ በሕገ መንግሥቱ የተዘረዘሩት የሰብዓዊ መብቶችም ከዓለም አቀፍ ሰነዶቹ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲተረጐሙ ያስገድዳል፡፡ ይህም አገሪቱ ለሰብዓዊ መብት ሰነዶች በተለይም ለመግለጫው የሰጠችውን ሰፊ ቦታ የሚያመለክት ሲሆን፣ አገሪቱ በመግለጫው የተዘረዘሩት ሰብዓዊ መብቶች የሚፈጸሙበትን ሕግጋት ቀርጻለች፤ ተቋማትም አደራጀታለች፡፡ ቀሪው የአገራችን የቤት ሥራ መብቶች በተጨባጭ እንዲፈጸሙ ማስቻልና ያላትን የሰብዓዊ መብት አያያዝ መዝገብ ማሻሻል ነው፡፡ በዚህ ረገድ በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ወደ ሥራ የተገባበትን ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርኃ ግብር በተጨባጭ መፈጸም፣ በተግባር የሚስተዋሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መቆጣጠርና ሰብዓዊ መብት ለመጠበቅ የተቋቋሙ ተቋማት ገለልተኝነታቸውን በጠበቀ መልኩ ትርጉም ያለው ሥራ እንዲሠሩ ማስቻል ይጠበቅባታል፡፡ ዲሴምበር 10 ቀን 2014 የተከበረውን የሰብዓዊ መብት ቀን አገራችን ስታከብር እስካሁን የተሠሩትን ተቋማዊ ሥራዎች ከማድነቅ ጐን ለጐን ለሰብዓዊ መብቶች በተጨባጭ መከበር ቁርጠኛ አሠራር የምትዘረጋበት ሊሆን ይገባል፡፡

ከአዘጋጁ፡- ጸሐፊውን በኢሜል አድራሻቸው getukow@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡